# አስረሽ ምችው!የቁም ተዝካር(ተስካር)

ቅጥ ባጣ፣በተሞላቀቀ፣ደንታና ይሉኝታ ቢስ በሆነ ተግባር ወይም ፈንጠዝያ ላይ ሰው ከተሰማራ ድርጊቱ አስረሽ ምችው በሚል ቃል ይገለጻል፡፤በአገራችን ልማድ አንድ ሰው በበሽታ ወይም በዕድሜ ብዛት መሞቻ ቀኑ የደረሰ መሆኑን ሲረዳና ሲገነዘብ በቁሙ ጥሎ የሚሄደውን ንብረቱን የሚያወርሰውን አውርሶ የተረፈውን በቀሳውስት ጸሎትና በለቅሶ የታጀበ ድግስ ደግሶ ከወዳጅ ዘመድ ጋር የመሰነባበት ግብዣ ካደረገ የቁም ተስካሩን አወጣ ይባላል።

ሰሞኑን ሁለቱንም አይነት ድግሶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያካሂያደው በስልጣን ላይ ያለው ህወሃት/ኢሕአዴግ ነው።ሁኔታውን በቅርበት የታዘበውና የግብዣው ተቋዳሽ የሆነው ወዳጄ ያካፈለኝን ለማካፈል እወዳለሁ።

ወዳጄን ደውዬ ሰሞኑን ምን አዲስ ነገር አለ?ብዬ ጠየኩት።እሱም ምን አዲስ ነገር አለ ብለህ ነው!የሰሞኑ እሩጫ የኢሕአዴግ የሩብ ዘመን በዓል ዝግጅት ነው ፣ለዚያም ሰፊ ግብዣ በአዲስ አበባ ብቻ ብዙ ሺህ ሰው ተጋብዟል፣እኔም አንዱ ነኝ።በቦታው ተገኝቼ ያየሁትን ጉድ ብነግርህ ይሻላል አለኝ።እንዴት በዚህ ጊዜ ብዙ ሚሊየን ሕዝብ ተርቦ በሚረግፍበት ወቅት መንግሥት ሃያ አምስተኛ ዓመቱን ብዙ ወጭ አውጥቶ ያከብራል አልኩት፤ያለው እኮ ለሥልጣኑ የሚጨነቅ እንጂ ለአገርና ለሕዝብ የሚያስብና ይሉኝታ ያለው መንግሥት አይደለም ይልቅስ ስለግብዣው ልግለጽልህ አለና ወደ ግብዣው አመራ።

የድግሱ ዝግጅት ከወራት በላይ የፈጀ ሲሆን ብዙ ሚሊየን ብርም የወጣበት ነው።በሚሊኒየሙ አዳራሽ ግብዣ የተጋባዙት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ ለስርዓቱ ለሚቀርቡትና በጥቅም ለተሳሰሩት ግለሰቦች፣ሃብታምና የታወቁ ሰዎች እንዲሁም ያገር ውስጥ ነጋዴዎች ሲሆኑ በሌላ ቀንና በሌላ ቦታ የውጭ አገር የዲፕሎማሲ ልዑካንና ከፍተኛ ባለሥልጣኖችም ተጠርተው የደስታውና የቁም ተስካሩ ተካፋዮች ሆነዋል ሲል አጫውቶኛል።

በግብዣው ላይ የተገኙት በተለይም የነጋዴዎቹ ማህበረሰብ በብዛት የሚተዋወቁ ናቸው፣እኔም አብዛኛዎቹን አውቃቸዋለሁ፤መደበኛ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ስለዝግጅቱ ሁሉም በመገረም መተቸት ጀመረ፤መፈራራት የሚል ነገር አልነበረም፡፤አንዳንዱ እንዴት በዚህ አገር በተራበበት ጊዜ ይህን አይነት አስረሽ ምችው ድግስ ይደገሳል? ሲል ሌላው ደግሞ አስረሽ ምችው ፈንጠዝያው ላለፉት 25 ዓመታት ካለምንም የስልጣን ተካፋይ ብቻውን በጉልበት በመግዛቱ የተሰማውን ደስታ ለመግለጽ ሲሆን ከዚያ ጀርባ ደግሞ ባለበት ውጥረትና በገጠመው ሕዝባዊ ተቃውሞ ለመሰንበቱና በስልጣን ላይ የመቆየቱ ዋስትና በሚያጠራጥር ሁኔታ ላይ በመሆኑ የቁም ተስካሩን ማውጣቱ ሊሆን ይችላልና እንዲህ ያለ ጥሪ ሊደርሰን ስለማይችልና የመጨረሻም ሊሆን ስለሚችል ሆድና ግንባር አይሸሸግም ነብስ ይማር እያልን እንብላ የሚል አስቂኝና አሳዛኝ ትችት ሲሰነዝር ሌላውም የሕዝብ ገንዘብ ነው፣በራሳችን ገንዘብ የተዘጋጀ እንጂ ኢሕአዴግ ከየት አመጣው?ሲል ሁላችንም በአዎንታ ተቀብለን እየተሳሳቅን የቀረበልንን መብላት ጀመርን።ሰው የልቡን አውጥቶ መናገር ጀምሯል፣ፍርሃት የሚባል ነገር የቀረ ይመስላል ሲል አቃረጥኩትና ለምን ግብዣውን ተቀበልክ? አልኩት።እሱም መልሶ ሰበብ ፈጥሬ ለመቅረት አስቤ ነበር ግን ብቀር ከተቃዋሚ ጋር አሰልፈው ችግር ስለሚያመጡብኝ በፍርሃት ሳልወድ ሄጃለሁ ግን መሄዴን ወደድኩት፤ብዙ ለማየትና ለመታዘብ ለአንተም አሁን ሁኔታውን ለመግለጽ ቻልኩ በማለት የታዘባቸውን ነገሮች መግለጽ ጀመረ። "የአንዳንዱ አበላል እህል ቀምሶ የማያውቅ ይመስላል፣የሰው ልጅ እንዲህ በአደባባይ እንደአውሬ ሙዳ ሙዳውን እየቆረጠ ሲጎሰጉስ ማየቱ ያስፈራል።በዱሮ ጊዜ ሰው ግብዣ ቦታ ሲሄድ ግምት ውስጥ ላለመግባት ከቤቱ ቀማምሶ አሞቱን ገታ አድርጎ ነበር፣አሁን ግን የዚያ ተቃራኒ ሆኗል፤ምናልባትም ድግሱን በማሰብ ለሁለት ቀናት ሳይበላ ያደረ ወይም በጧቱ እንግሊዝ ጨው ጠጥቶ ሆዱን አጥቦና ምናምኑን አራግፎ የመጣ ይመስላል።ይሉኝታ የሚባል ነገር በቦታው የለም፤ዳሩስ ይሉኝታቢስ በሆነ መንግሥት የሚተዳደር አገርና የሚዘጋጅ ድግስ ላይ ምን ይሉኝታ ይኖራል ብለህ ነው?ሲል በብስጭት ሁኔታውን ገለጸልኝ።

ወዳጄ በዚህ ብቻ አላቆመም፣ የግብዣው ቦታና አካባቢው ምን እንደሚመስል እንዲህ ሲል ገልጾታል፣- ወደ አዳራሹ በሚወስደው ዙሪያ ገጠም መንገዶች ፖሊስ ተደርድሮ ደሃ የሚባል ዝር እንዳይል ይከላከላል።ሌላውም  ያልተጋበዘው መንገደኛ በአዳራሹ አካባቢ መቆምና መታዘብ የማይችል ሲሆን አካሄዱን ፈጠን ፈጠን አድርጎ ከቦታው እንዲርቅ ይገደዳል።ተጋባዡ የግብዣ ጥሪውን እያሳዬ ይገባል፤ ከዚያ ውጭ አካባቢው ለሌላው ኢትዮጵያዊ የባእድ አገር መሬት ሆኖበት ውሏል።እኔም ወደ አዳራሹ ስገባ፤የአስተናጋጁ ብዛት፣ወከባና የተጨናነቀው መቀመጫ፣የተለያየው የመጠጥ አይነት፣የሰው ብዛትና ሙቀት፣የሙዚቃው ጫጫታ አንድ ላይ ተደራርቦ የማየው ሁሉ ቅዠት መሰለኝና ዞረብኝ።አዲስ አበባ ውስጥ ያለሁ አልመሰለኝም፤ ሃብታሙ ለሆዱ ሰልፍ ገብቶ ሳየው እራሴን ታዘብኩት።የክት ልብሱን የለበሰው ተጋባዥ ተጀንኖ ሲራመድ፣ሴቷም ተሽቀርቅራ ስትኮፈስ(አብዛኛዎቹ የትግሬ ሹርባ የተሰሩና በወርቅ ያጌጡ ሲሆኑ የመሃል አገር ሴቶችም መስሎ ለማደር ሳይሆን አይቀርም እንደዛው ለብሰዋል) የደሃና በርሃብ ብዙ ሚሊየን ወገኖቹ የሚያልቅበት አገር ዜጎች አይመስሉም። እንዲህ ሰው የበዛበትና ሰፊ ዝግጅት ያለው ግብዣ ሳይ በህይወቴ የመጀመሪያ ጊዜየ ነው።በሌላም በኩል መጨናነቁን አይቼ አዳራሹ ቢደረመስ ምን ይውጠኛል እያልኩ በስጋት ሳወጣና ሳወርድ የምግብ መስተንግዶው ሰዓት ደረሰ።በልቤ ነፍስ ይማር እያልኩ የቀረበልኝን በንዴትም በእልህም እንክት አድርጌ በልቼ፣አንድ ማወራረጃ ከወሰድኩ በኋላ አዳራሹን ጥዬ ወጣሁ።

ወዳጄ በመቀጠል፤ይኸ መንግሥት ቀላል አይምሰልህ የሰውን ስነልቦናና ደካማ ጎን በደንብ ተረድቶታል፡፤ሆዳሙን በግብዣ፣ሴሴኛውን በዝሙት፣ሰካራሙን በአልኮል፣ቦታ ፈላጊውን በኩርማን መሬት፣ ቤት ፈላጊውን በኮንዶ፣ ሙሰኛውን(ጉቦኛውን) በገንዘብ፣ ጎሰኛውን በዘፈንና በሹመት ተብትቦ አስሮታል።አንዳንዱንም የወንጀል ተካፋይ አድርጎ ማኖ አስነክቶት በፍርሃት ተሸማቆ ታማኝ አገልጋይ እንዲሆን አድርጎታል።እውነተኛ ተቃዋሚውና አገር ወዳዱ ግን የጥይት እራት ወይም የእስርቤት ሲሳይ ሆኗል።ካለ በኋላ በመቀጠል

በአዲስ አበባ በግንቦት ሃያ ቀን ሰበብ በተደረገው ጣምራ ድግስ በሚሊኒየም አዳራሽ ተብሎ በሚጠራው ሰፊ አዳራሽ ስድስት ሺ(6000)ሰው ሲጋበዝ ለእለቱ ለቁርጥ ብቻ 60 በሬ ታርዶ እንደቀረበ ከዝግጅት ክፍሉ ሠራተኞች ሾልኮ የወጣው ማስረጃ ያረጋግጣል፡በማለት በሂሳብ ወደተደገፈው ዝርዝር ገባ።ለእያንዳንዱ በሬ በአማካይ ሃምሳ ሽህ (50,000)ብር በጠቅላላው ሶስት ሚሊየን ብር(3,000,000) ወጥቷል ማለት ነው፤ይህ ደግሞ በተመጋቢው ቁጥር ከተሰላ አንድ በሬ ለመቶ ሰው ይሆናል ማለት ነው፣በገንዘብ ለእያንዳንዱ ሰው የአምስት መቶ(500)ብር ቅርጫ ይደርሰዋል ማለት ሲሆን ከዚያ ውስጥ አጥንቱና ሌላው ቀርቶ በአሁኑ ገበያ ከ300(ሦስት መቶ ብር )በላይ የሚያወጣ ምርጥ ቁርጥ ሥጋ ይደርሰዋል ማለት ነው።ለልዩ ልዩ መጠጥ የወጣው ወጭ ምን ያህል እንደሆነ በቅጡ ባይታወቅም በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ ሳይወጣ እንዳልቀረ መገመት ኣያቅትም።በአገር ውስጥ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡና ለውጭ አገር እንግዶች የተለየ ግብዣ ሲደረግ ወጭውም እንደዚያው የብዙ ሚሊየን ዶላር እንደሚሆን ይገመታል፣ምክንያቱም እነሱን በቁርጥ ሥጋ መሸኘት ስለማይቻል የግዴታ የፈረንጅ አገር ምግብና መጠጥ ማቅረብ ስለሚያስፈልግ ከውጭ አገር በውጭ ምንዛሪ የሚሸመት ነው።ከአዲስ አበባ ውጭ በጠቅላላው የአገሪቱ ክፍሎች(ክልሎች)እንደአቅሙ ተመሳሳይ አስረሽ ምችውና የቂም ተስካር ድግስ በመካሄድ ላይ ነው።ላለፉት አስር ቀናት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በዚሁ ድግስ ዝግጅት ላይ በማተኮር መደበኛ ስራቸው ተቋርጦ ነበር።በቀጣይነት ሌት ተቀን ሲሰሩ የከረሙት የጸጥታና የፖሊስ እንዲሁም የቤት አፍራሽ ግብረሃሎች ናቸው።

ለመሆኑ አንተስ ባለህበት አገር ምን አዲስ ነገር አለ?እውጭ አገር ካላችሁት እኮ ብዙ እንጠብቃለን።እንደእኛ የቂም እስረኞች አይደላችሁም፤ለመሰብሰብና ለመወያየት ፣በነጻ ለመንቀሳቀስ ትችላላችሁ።ያገራችሁንም ሁኔታ ለዓለም ሕዝብ ልታሰሙበት የምትችሉበት መንገዱ ብዙ ነው።እዚህ ያለነው መንቀሳቀስ አንችልም፤የፖለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶችም በረጅም ገመድ እንደታሰረች ዶሮ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት አቅጣጫና እርቀት የተወሰነ ነው፤ከዚያ ሊያልፉ

አይችሉም፣ድፍረቱም የላቸውም።አንዱ ሲጠቃ ሌላው በዝምታ ያያል፣እሱም በተራው ይደቆሳል። አይችሉም፤በተጨማሪም ህብረት የላቸውም፣እርስ በርሳቸው ሲሻኮቱ ነው የሚታዩት።ሌሎቹም በተቃዋሚ ስም በመንግሥት ድጎማና ፈቃድ የሚንቀሳቀሱ አሳሳቾች ናቸው፤ካለ በኂላ ስለውጩ ትግል እንድነግረው ጠየቀኝ።እኔም ከአገር ቤት ልዩነቱ የቦታ እርቀት ከመሆኑ ባሻገር በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ እንደሆነ፤ድርጅቶች እርስ በርሳቸው የሚጠላለፉና አንዱ ሌላውን እያወገዘ የሚሄድ፣አንድና ሁለት ሰው ይዞ ድርጅት ነኝ በማለት የየራሱን ዘውድ በኪሱ ይዞ የሚዞር፣እንተባበር ሲሉት እራሱን እያሳበጠ ጥሪውን የማይቀበል፣የተዝረከረከ ተቃዋሚ የበዛበት እንደሆነና በሌላውም በኩል አብዛኛው ለራሱ ኑሮ የሚጨነቅ፣ስለአገሩ ደንታ የሌለው፣የሚፈልገውን  ቦታና ቤት ለማግኘት ከመንግሥት ባለስልጣኖች ጋር የሚያፈደፍድ፣ለአገር ጉዳይ ከሚሰበሰበው ይልቅ በድግስና አስረሽ ምችው የሚተራመሰው እንደሚበዛ አስረዳሁት።በየጊዜው በመንግሥቱ አምባሳደሮች ተመሳሳይ ዝግጅት በሚስጥር እየተዘጋጀ ሆድ አደሩ እንደሚሳተፍ ስነግረው ታዲያ ኢሕአዴግ ለዘላለሙ ይኖራል በለኛ! ሲል በመገረም ስሜት ውስጥ እንዳለ ጨዋታችንን ሳንጨርስ የስልክ መስመራችን ተቋረጠና ተለያየን።

የሰማሁት ሲረብሸኝ አመሸ፤እንዴት መንግሥት ነኝ የሚል አካል፣ እንደሰው ማሰብ የሚችል ሰው በገዛ አገሩ ላይ ይህን አይነት በደልና ግፍ ይፈጽማል?በሚሊየን የሚቆጠረው ወገኑ በርሃብ ስቃይ ሲረግፍና የውጭ አገር በጎ አድራጊዎች እርዳታ ለመሰብሰብ ሲሯሯጡ፣በየአገሩ ቴሌቪዥን መስኮት ላይ የሞት ሲቃ የሚያጣጥሩ ህጻናትና አዛውንት እየታዩ እርሃብ መኖሩን የሚክድ መንግሥት ይህን አይነት አስረሽ ምችው ድግስ ማድረጉ ተገቢና የጤና ነው?ወይስ ወዳጄ እንዳለው ተስፋ በመቁረጥ የተዘጋጀ የቁም ተዝካር! አልኩና  ሆነም ቀረም ታሪኩን ለሌላው ማካፈል አለብኝ አልኩና በዚህ መልክ ለማቅረብ ወሰንኩ።

የህወሃት/ኢሕአዴግ ሃያ አምስተኛው ዓመት ድግስ የመጨረሻው እንዲሆን እንተባበር!!

አገሬ አዲስ